# የጥላቻ ፖለቲካ እንደራሴዎች
# የወያኔ ወዶ ገባ ሥውር ረዳቶች!

ከአቶ ሰውየው

*"ኢትዮጵያ በረጅም የታሪኳ ሂደት የተለያዩ ብሄረ-ሰቦች መልካሙን፣ ክፉዎን ጊዜ አብረው በማሳለፍ <u>የጋራ የሆኑ እሴቶችና አንድነት ማለትም ኢትዮጵያዊነትን ፈጥረዋል። ኢቲዮጵያዊነት ስንል ለብዙ ሺህ ዓመታት አብረው በመኖርና በመዋለድ በጋራ ያዳበሩትን የአንድነት መግለጫዎቻቸውን፣ ማለትም እንደ ድርና ማግ የሚያስተባብራቸውን ማለታችን ነው።</u> (የተሠመረው በእኔ) "*

ከዚህ በላይ ያለው ጥቅስ የተገኘው "ፍካሬ" ከሚባለው በኢሕአፖ ታትሞ የሚወጣ ጥናታዊ የትንተና መጽሔት (ልዩ ዕትም ቅጽ 16 ቁጥር 1 — መስከረም 2001) ነው።

ወያኔዎችና መሰሎቻቸው ለራሳቸው እንዲያመቻቸው ኢትዮጵያዊነትንና ታሪክን ክደው ሕዝብን ሊያጫርስ የሚችል ሥርዓት ዘርግተው ባሉበት በአሁኑ ወቅት፤ ወያኔን እንቃወማለን የሚሉን በሌላ ጽንፍ የተሰለፉ አንዳንድ ጨለምተኞች ደግሞ ሀገር በማዳን ስም እየማሉና እየተገዘቱ ኢትዮጵያዊነትን የሚፈታተን የትግል ስልት ይዘው ሕዝባዊውን ትግል የወያኔ ወጥመድ ሰለባ ሊያደርጉ እየተሯሯጡ እያየን ነው።

በዘረኝነት፤ በጎጠኝነት፣ በትምክህተኝነትና በጥላቻ ላይ የተመሠረተ <u>የማግለል</u> ፖለቲካ ጨዋታ፤ የሰውን ልጅ በአስከፊው ባሕሪይው ማለትም በዕብሪት ተነፋፍቶ፤ ሰው ከሰው እንደ ሰው ተከባብሮ አብሮ ለመኖር የሚያስችለውንና ሚዛናዊነትን የሚያዳብርበትን ውስጠ ሕሊና አጫጭቶ የስብዕና መለዮውን በቁሙ የሚገድልበት በሽታ ነው። በእኔ ዕምነት የዓዕምሮ ንቅዘት ዕብደትም ነው እላለሁ። በመሆኑም ይህ በሀገራችን የፖለቲካ አድማስ ብቅ ብሎ የሚታየው የጥላቻ ፖለቲካ የሰው ልጅ በቅዠት ዓለም ተቸንክሮ፤ የራሱን ወገን አርዶ ከመብላት ወደ ኋላ የማይል ጭፍን እንዲሆን የሚያደርገው ጥቂት ህመምተኞች የሚገፉት ቅዠት ነው ባይ ነኝ።

የዚህ ጽሑፍ ዓላማ "ግርግር ለሌባ ያመቸዋል" እንዲሉ ሀገር እያፈረሰ ባለው የወያኔ መንጋ ላይ ትኩረት በማድረግ ኃይልን አፈርጥሞ በቆራጥነት የሚጠይቀውን መስዋዕትነት ከፍሎ ሀገር የማዳን ርብርቦሽ ከማድረግ ይልቅ በተቃዋሚው ጎራ ውስጥ ግርግር የሚፈጥሩ፤ ለማንም ተጠያቂ ያልሆኑ የጥፋት እንደራሴዎች ሊቻቻሉ የሚችሉና በጊዜው አንገብጋቢ ያልሆኑ ጥቃቅን ቅራቄዎችን ከሚገባቸው በላይ በማግዘፍ ድርጅት እያፈረሱ ከፊታችን ሲከምሩ፤ የአንድነት ኃይሉ ዓይን ለዓይን እንዳይተያይ የጥርጣሬን የውሸት መርዛቸውን ሲረጩ ማየቱ እንዲያበቃ፤ ሀገር ወዳድ ወገኖች በዝምታና በይሉኝታ መመልከቱን ትተን ቆማጣውን ቆማጣ፤ የሚያስነውረውን ነውር፤ በማድረግ ድርጅቶችና መሪዎቻቸውን ተጠያቂ እስካላደረግን ድረስ ወያኔ እንደቀለደብን እንደሚኖር ለማሳሰብ ነው።

ስለሆነም እስኪ ከታዘብኳቸውና ኃላፊነት በጎደለው ሁኔታ በተቃዋሚው ጎራ ውስጥ መናቆርን ከሚያስፋፉ በኃላፊነት የምጠይቀቸውን ከነምክንያቱ ላስቀምጥ።

1. **የኢሕአፓ አንጃኞች የመጀመሪያ ዓመታቸውን በዚህ ሳምንት እንደሚያከብሩ አስታውቀውናል።**

*በመጀመሪያ ኢሕአፓ ብለው ራሳቸውን ለመጥራት ምንም ዓይነት የሞራልም ሆነ ሕጋዊ መብት የሌላቸውና በኔ ግምት ንብረት የዘረፉ ተራ አጭበርባሪዎች ናቸው። በዚህም ልንጠይቀቸው ይገባል። የድርጅታችውን የብዙሃን ድምፅ ጠቅጥቀው ወጥተው ዴሞክራሲያዊ ኢሕአፓዎች እኛ ነን ሲሉን "<u>ማንም የሚጠይቀን የለም የፈለግነውን እናደርጋለን</u>" እያሉን ስለሆነ በእኔ ግምት ለሕዝብ ያላቸውን ንቀት የሚያመለክትና ፀረ-ዴሞክራሲዎች መሆናቸውን ካለጥርጥር ያረጋገጠልኝ ነው። ሌላውን ተወት ላድርገውና እስኪ ዓመታቸውን ሊያከብሩ ሲነሱ ሀገር ወዳዶች ልንጠይቀቸው የሚገባው ሕሊና ካላቸውና የሚመልሱልን ከሆነ፤<u>ለመሆኑ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ትግል በአንድ ዓመት ውስጥ ምን አበረከታችሁ?</u> የሚለው ነው።*

*ዓመቱን ሙሉ እንደታዘብኳቸው ለኢትዮጵያ ሕዝብ ትግል ምንም አላበረከቱም። ዚሮ። በወያኔ ላይ ቅስቀሳ ከማድረግና ከመታገል ዓመቱን ያሳለፉት ኢሕአፓንና ቆራጥ መሪዎቹን በመታገል ብቻ ነው። ከብዙ በጥቂቱ ለመዘርዘር፦*

*ሕገ-ወጥ በሆነ መንገድ በወሰዱት ራዲዮ ፀረ-ኢሕአፓ ቅስቀሳ አድርገዋል። በወያኔ ላይ ቆራጥ አቋም ያላቸውን መሪዎች ማለትም ኢያሱ ዓለማየሁ፣ ፋሲካና ገነት ግርማ ላይ የማያቋርጥ የውሸት ቅስቀሳ እያደረጉ ነው። ይህንንም በሳምንት ሁለት ቀን በሚከፍቱት የፓልቶክ መድረክ በጊዜው አንገብጋቢ ጥያቄ ላይ ከመወያየትና አቋም ከመያዝ ይልቅ በፀረ-ወያኔነታቸው ወደር የሌላቸውን ኢሕአፓዎችንና መሪዎቻቸውን ስም የማጥፋት ዘመቻ ላይ መሰማራታቸውን እየታዘብን ነው። ለመሆኑ ማንን ለመጥቀም?*

*ብዙ ወገኖች የተዋደቁበትን ዓላማና ታሪክ ክለሳ በሰፊው ተያይዘውታል። እንወደድ ብለውም ለኢትዮጵያዊነት ምንም ክብር ከሌላቸው ፀረ-ኢትዮጵያ ኃይሎች ጋር ሲጎናበሱ ተስተውለዋል። እንደምሳሌም የወያኔ የወታደር መሪ ከነበረው አረመኔ፤ ለሠራው ጥፋት እንኳ ምንም ሲጸጸት ያልተሰማ ሥዬ አብራሃን በዋሺንግተን ዲሲ አካባቢ ለሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ስብሰባ እንዲገኙለት በዘረፉት ራዲዮ ቅስቀሳ አድርገውለታል። ውሎአቸው ቀይ ሽብር ይፋፋም ከሚሉ ድምባጕሞች ጋር ነው። ለዚህም ሕሊና ያለው ወገን ሊጠይቀቸው ይገባል ባይ ነኝ።*

*በቅርቡስ ኢትዮጵያን እንደ ባዕድ ሀገር ለሚመለከተው ለአነጉ ሌንጮ ለታ መድረክ ሰጥተው የጥላቻ መርዙን በመድረካቸው ሲያንቆረቁልን፤ በመድረካቸው ላይ የተሰበሰበው ሕዝብ በቅጡ እንዳይጠየቅ ጠያቂዎችን ሲያባርሩ የዋሉበትን ቀን እናስታውሳቸውና ማንን ለመጥቀም ነው ብለን ልንጠይቃቸው ይገባል? የኢትዮጵያን ሕዝብ ትግል ግን ለመጥቀም አይደለም። ወራዳ ማፈሪያዎች ናቸውና!*

በነገራችን ላይ በቅርቡ ከውስጥ አዋቂዎች እንደሚሰማው ከሆነ በሁለቱ መሪዎች መካከል ወያኔ ጋር እንግባና አንግባ ፍትጊያ መኖሩና አንጃው ሌላ አንጃ በቅርቡ ሊያበቅል ይችላል የሚሉንም አሉ። ለአሉባልታ ቦታ ባልሰጠውም በዚህ ላይ እንዲገነዘቡልኝ የምሻው ድሮም ሌቦች አንድነታቸው እስኪሰርቁ እንጂ በክፍያ ጊዜ መፋጀታቸው አይቀርም። አንጃው መበታተኑ አይቀሬ ነው። ምክንያት ብትሉኝ አንድ ወጥ አስተሳሰብ ያላቸው አይደሉምና። ያሰባሰባቸው የግለሰቦች ቁንባ ጥላቻ ብቻ እንጂ በመተክል ተገናኝተው ለኢቲዮጵያ ሕዝብ ትግል አስበው አልነበረም። ተገንጥለው ወጥተውም የራሳቸውን ፓልቶክ የከፈቱ ሰሞን ኢሕአፓ እንዲፈርስለት የተሳለ ፀረ-ኢትዮጵያዊና ወያኔ ሁሉ በመድረካቸው ተሰባስቦ ሲውል እንደነበር አንርሳው። ሁሉንም ያገናኛቸው ኢሕአፓ ይፈርሳል የሚል ቅዠት ነበር እንጂ ተጣጥመው ወይም ለኢትዮጵያ ሕዝብ ትግል ቅንጣት ያክል ለማበርከት አልነበረም።

ሌንጮ ለታ የቀይ ሽብር በኦሮሞ ሕዝብ ላይ ብቻ የተካሄደ እንደሆነና ኢሕአፓን ደግሞ የአማራ ነፍጠኛ ድርጅት ነው ብሎ ሲያወራ የማያፍር ውሽታም ነው። በቀይ ሽብር ያለቀው መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ነው። ያም ከላይ በጥቅሱ ያስቀመጥኩትን አባቶቻችን ያስረከቡንን ኢትዮጵያዊነት አሻሽለን፤ ማለትም ከጥቂቶች መጫወቻነት የብዙሃኑ እንድትሆን ሁሉም የተዋደቀበት ድርጅት መሆኑን ሲክድ የሚያመለክተኝ ያኔም በተሳሳተ የታሪክ ጎዳና ይጓዝ እንደነበር ብቻ ነው። አንጀኞች ጥላቻን አንግበው ኢትዮጵያዊነትን ከማይፈልጉ እንደ ሌንጮ ያሉ የታሪክ አተላዎች ጋር መሰለፍን መርጠዋልና እንፈርጃቸዋለን።

በትግላችን ውስጥ ተጠያቂነትን መገንባት ገዜው አሁን ነው። ከኛ በላይ አታጋይ የሚሉንና፤ ለሕዝብ ንቀት ያላቸው፤ ትግሉንም ሊነግዱበት የተነሱትን ልንታገላቸው ይገባል።  ለመሆኑ እናንተ እነማናችሁ ብለን ካልጠየቅን እነሱ የሕዝቡን ትግል ያስበላሉ እላለሁ።

2. emaye_3: thank you enderasse
   emaye_3: shewa bere 20,000 hodamoch amara, gurage etc  ke-4,000,000 ye-tigray tetekamiwochn mawedader ayichalim

   አዎ ዘረኝነትን ለማጥፋት ዘረኞች እንድንሆን የሚጋብዙን፤ ወያኔን እየተቃወምን እኛም እንደወያኔዎች አንድን ዘር በሀገራችን ላለው ጥፋት ሁሉ ተጠያቂ እናድርግ የሚሉን የጥፋት እንደራሴዎች ድምጻቸውን ከፍ አድርገው እየተንጫጩብን ነው። ወያኔ አማራ ብሎ በመላ ሕዝብ ላይ ዘምቶ ሰው በአማራነቱ ከገደል እንዲወረወር አድርጓል። በነገራችን ላይ ከላይ አንጀኞች አብረው የሚያጫፍሩትም ዘረኛው ሌንጮ ለታ ይመራ የነበረው ኦነግ ለብዙ ጥፋት ተጠያቂ ነው። ይህ በእንዲህ እያለ አሁንም ለማንም ተጠያቂ መሆን የማይፈልጉ፤ የመንደር ሰንበቴ እንኳን መምራት የማይችሉ ወገኞች ወያኔን ለመቀወም መላው የትግራይ ሕዝብ ላይ መዝመት አለብን ብለው በየፓልቶኩ የሚቀደዱ በእኔ ግምት ባለጌዎችን ማንም ይሁኑ ማን ዝም ብለን ልናደምጣቸው አይገባም።

የሚወስዱን ከሌላ አጣብቂኝ ነውና ልክ አለመሆናቸው ሊነገራቸው ይገባል። በሚያሳዝን ሁኔታ አንዳንዶቹ የከፍተኛ ትምህርት ተምረዋል የሚባሉም ይገኙበታል። ይህንን በሚመለከት በቅርቡ ብዙ ወገኖች ተቸተውበታል። አቶ ቤልጅግ አሊ "እኔም ትግሬ ነኝ" በሚል የጻፉት አስደስቶኛል። ትግላችን በስሜት ብቻ ስይሆን በመተክል ላይ የተመሠረተ እንዲሆን የጠነከረ ስሜት ያላቸው ወገኖች መኖራቸው አኩርቶኛል።

3. የጊዚያዊ የኢትዮጵያ የስደት መንግሥት መሥርተናል የሚሉቱ በአንድ ራዲዮ ብቅ ብለው ተደብቀዋል። "አማርኛውን መምረጥ ጋሪው ፈረሱን እንዳይቀድም" በሚል የተጻፈ ጥሩ አስተያየት በደብተራው፤ በአሲምባና፣ ኢትዮላዮን የመሳሰሉት ድረ-ገጾች ላይ ያንብቡ። ምናልባትም የስደት መንግሥት ላሉት ጥሩ መልስ ነው። ህብረተሰቡ ግን እናንተ እነማናችሁ ብሎ መጠየቁ ተገቢ ነው፤ አይቀሬም ነው እላለሁ።

4. በነገራችን ላይ ስለጊዛዊ መንግሥት የታወጀው በአለም አቀፍ የኢትዮጵያ ሴቶች ድርጅት ራዲዮ ጣቢያ ላይ ነበር። አለም አቀፍ የኢትዮጵያ ሴቶች ድርጅት አባላት በተመሠሪተው የስደት መንግሥት ያምናሉ ማለት ነው? በነሱም ውስጥ ብዙ መናቆር እንዳለ የሚያመላክቱ ሁለተኛ አለም አቀፍ የኢትዮጵያ ሴቶች ድርጅት ስም የያዘ የፓልቶክ ክፍል ከተከፈተ በርካታ ሳምንታትን አሳልፎአል። ከአህያ የዋለች ጊደር እንዲሉ የአንጃኞች ብሽታ ገብቶባቸው ይሆን?

5. ሕብረትን ሕገ-ወጥ በሆነ መንገድ አፍርሰው "ጥምረት ወይም ሞት" ያሉንስ ግብዞች? የበላቸው ጅብ ለመሆኑ ጮኋል? የሰማስ አለ የሚነግረን?

**ለማጠቃለል፦**

ከዚህ በላይ በጣም በጥቂቱ ለላንቲካ ያክል በኢትዮጵያ ሕዝብ ስም የሚነገደውን ባቀርብም ይሂም ብቻ አይደለም። ላለፉት 17 ዓመታት ወያኔ እንዲቀልድብን የረዱትን በሙሉ አውጥተን ብንዘረዝር ስንክሳር እንጽፋለን። በሕብረተ-ሰባችን ውስጥ እንመራለን እያሉን ብቅ የሚሉትን እነማን እንደሆኑ፤ የሕግ የበላይነትን ማክበር የሚችሉ ወይም የማይችሉ ለመሆናቸው፤ ታማኞች ወይም የክህደት ያለፈ ታሪክ ይኑራቸው ወይ አይኑራቸው፤ በወያኔ ያላቸው ቀራጥነት ሳይመረመርና ማንነታቸው በደንብ ተጣርቶ ሳይረጋገጥ ልባችንን ከፍተን በየዋህነት እጃችንን እየዘረጋን ስንት ጊዜ እንመታ? ከዚህስ በኋላ ይብቅን ማለቱ ተገቢ አይሆንም? ኸረ የሕዝብ ትግል መቀለጃ የሚያደርጉትን ሁሉ ልብ ያለው ልብ ይበልልኝ!

ወገኖች ዝምታውንና ገለልተኝነቱን ይዘን በይሉኝታ ከሁሉም እርቀን በመቀመጥና ነገር ዓለሙን ለጥቂት የጥላቻ አራጋቢዎች በመተው ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ወደ ሀገራችን ይመጣል ማለት ዘበት መሆኑን በመገንዘብ ቅን ሀገር ወዳዶች እኛም ያገባናል ማለት መጀመር ይኖርብናል። የሀገር ጉዳይ ለጥቂት እብዶችና ቡድኖች የሚተው አይደለምና። መሪዎች ነን ባዮችን፤ ድርጅቶችን ልናርቃቸውና ልናንፃቸው ይገባል። ትላንትና የሠሩትን ጥፋት ሳያምኑ ዘሬ አዲስ ድርጅት ይዘው ሲመጡ እናንተ ደግሞ እነማናችሁ? ማለት መጀመር አለብን። በግልጽ ታሪክ የሠሩትን፤ በፀረ-ወያኔነታቸው ያላወላወሉትን ማቀፍ መደገፍ፤ ሊያፈርሷቸው ከሚጥሩ ከውስጥም ሆነ ከውጪ ኃይሎች መከላከልም ግዴታችን ነው። ይሉንተኝነትንና ስሜታዊነትን ወደ ጎን ማድረግ ያሻል። በሀገር ቀልድ የለምና። ዶክተር ተሆነ አልተቶነ ባደባባይ ወያኔን ለመቃወም ትግሬዎች ላይ እንዝመት አይነት ነገር ሲዘምሩብን ዝም ብለን ማድመጡ ሊመጣ ለሚችለው አደጋ አለመናገራችን ራሱ ተባባሪነት ነው። እያንዳንዳችን፤ ወገን በትግሬነቱ፤ በአማረነቱ፤ በኦሮሞነቱ፤ በወላሞነቱ፣ ሲንገላታ እኔም ትግሬ ነኝ፤ አማራ፤ ኦሮሞ፤ ወላሞ ከሁሉም በለይ የኮራሁ ኢትዮጵያዊ! ማለት አለብን። በማንኛውም ዓይነት የሚገፋን ጠባብነት ሆነ ትምክህተኝነት ማጋለጥ የእያንዳዳችን ድርሻ ስናደርገው ኢትዮጵያዊነትን እናድናለን። በነገራችን ላይ የተማሩ የትግራይ ተወላጆችም ቢሆኑ የወያኔ ቡድን እያስፋፋ ያለውን የጥላቻ ፖለቲ ዝም ብለው በለዘብተኝነት ወይም በይሉንታ መመልከት በተዘዋዋሪ መንገድ ተባባሪነት መሆኑን ሊገነዘቡት ይገባል። እዚህ ላይ አቶ ጌታቸው ረዳንና መሰሎቹ፤ ሀቀኛ ኢትዮጵያውያን፤ በተግባር ወያኔን በማጋለጥ ለሚያደርጉት ሁሉ ሳላመሰግን አላልፍም።

ሌላው ደግሞ ለሀገራችን ሕዝብ የዴሞክራሲያዊና የሕግ የበላይነትን ለማምጣት እየታገልን ነው የሚሉን ድርጅቶችም ሆነ ቡድኖች ዴሞክራሲያዊነትንና የሕግ የበላይነትን የሚናንጸባርቁ መሆናቸውን በዕለት ተዕለት ተግባራቸው ማስመስከር ግዴታቸው መሆኑን እንዲያውቁት ማድረግ አለብን። ሕገወጥ በሆነ መንገድ ድርጅታቸውን አዳክመው አዲስ ድርጅት ነን ብለው ሲመጡ ወይግዱ ማለት እንጂ ማጀቡ ወደፊት ለሚመጠው አጣብቂኝ እኛም ተጠያቂዎች መሆናችንን አንርሳ!

እምቢኝ ለዘረኞች! እምቢኝ ለበታኞችና ለባንዳዎች!
ኢትዮጵያዊነት ያለጥርጥር በትግላችን ያብባል!

አቶ ሰውየው
ከሰሜን አሜሪካ
( ህዳር 5 ቀን 2001 November 14, 2008 )